# አብዮታዊት ኢትዮጵያ

25




ሚያዝያ ፴ — ፲፱፻፸፱ ዓ.ም.

ርእሰ አንቀጽ

# «የተራማጆች ኅብረት ይጠንክር»

የኢትዮጵያ ወዝ አደር ነቅቶና ተደራጅቶ ታሪክ ለጣለበት የአብዮት መሪነት ሚናው ብቁ ለመሆን ሲታገል ብዙ ዓመታት አሳልፏል ። በነዚሁ የትግል ዓመታትም ብዙ መሥዋዕትነት የተቀበለውን ያህል በንቃትና በድርጅት ጐዳና ላይ ብዙ ድሎችን ተጐናጽፏል ። በፊውዶ—ፋሽስቱ የኃይለ ሥላሴ መንግሥት አገዛዝ ሥር ታዳጊው የኢትዮጵያ ወዝ አደር መደብ በተጫነበትየጭቆናና የባርነት ቀንበር ንቃተ ኅሊናው ገና ዝቅተኛ ደረጃ ቢሆንም በሞያ ማኅበር ደረጃ ተደራጅቶ ጥቅሙን ለማስከበር ሲታገል ይህ ነው የማይባል ግፍና ስቃይ ደርሶበት ነበር ። ቢሆንም የኃይለ ሥላሴ ፋሽስታዊ አገዛዝ እየነቃ የሔደውን ወዝ አደር ግፊት መቋቋም ስላልተቻለው በሐቀኛ የወዝአደር መሪዎች አማካይነት የኢትዮጵያ ሠራተኞች አንድነት ማኅበርን መሥርቶ ነበር ።

የየካቲት ፲፱፻፷፮ ዓ.ም. አብዮት ሲፈነዳ የኢትዮጵያ ወዝ አደር ገና በሞያ ማኅበር ተደራጅቶ ማንሰራራት የጀመረበት ወቅት ስለነበረና የንቃተ ኅሊናውም ደረጃ የሙያ ማኅበር ንቃተ ኅሊና ደረጃ ስለነበርና ፓርቲ ስላልነበረው የአብዮቱን አመራር ሊጨብጥ አልቻለም ነበር ። ቢሆንም ከዚያን ጊዜ አንሥቶ እስካሁን ድረስ «ካለወዝ አደሩ ፓርቲ አብዮት ግቡን አይመታም» በሚለው ሳይንሳዊ ሐቅ እየተመሩ አብዮታውያን ይህንን የወዝ አደሩ ብቻ ሳይሆን የጠቅላላውን የኢትዮጵያ አብዮት ድክመት ለመወጣት ብዙ ታግለዋል ። ተሰውተዋልም ።

በዚህ የንቃትና የድርጅት ትግል የኢትዮጵያ አብዮታውያን ሁለት መሠረታዊ ዓላማዎች ለመከተል ሞክረዋል ። የወዝ አደሩን የሞያ ማኅበር በሚገባ ለማጠናከርና የወዝ—አደሩን ተሳትፎ ለማሳደግ ታግለዋል ። በዚያው ልክ ደግሞ የወዝ አደሩን ፓርቲ ለመመሥረት የኢትዮጵያ አብዮታውያን በሙሉ ከፍተኛ ተጋድሎ አካሒደዋል ።

በነዚህ ሁለት የተያያዙ የትግል መስኮች በዚህ በያዝነው ዓመት ከፍተኛ ድሎችን ተጐናጽፈናል ። የቀድሞውን ኢ.ሠ.አ.ማ ከቍጥጥራቸው ሥር አድርገው ለፀረ—አብዮት ተግባር ሲያሠልፉት የነበሩትና በወዝ አደሩ የመንቃትና የመደራጀት ጥረት ላይ ታሪክ ምንጊዜም የማይረሳው ወንጀል ሲፈጽሙ የነበሩት የኢ.ሕ.አ.ፓ ሰርጎ ገቦች ከወዝ አደሩ እየተመነጠሩ ወጥተዋል ። የነሱ መፈንጫ በነበረው ኢ. ሠ. አ. ማ. መቃብር ማይ በኢትዮጵያ ወዝ አደሮች መራራ ትግል በአብዮታውያን መስዋዕትነትና ደም የመላ ኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር ተቋቁሟል ። የመ. ኢ. ሠ. ማ. መቋቋም ከአምናው ሜይ ዴይ እስከ ዘንድሮ ባለው ጊዜ ውስጥ የተጐናጸፍነው ከፍተኛ ድል ነው።

ነገር ግን ምንም እንኳን እጅግ መራራና መሥዋዕትነት በተሞላበት ትግል የተገኘ ድል ቢሆንም የመ. ኢ. ሠ. ማ. መቋቋም የትግላችን መጨረሻ ሆኖ የሚያዝናናን ጉዳይ አይደለም ። መ. ኢ. ሠ. ማ. የሞያ ማኅበር እንደመሆኑ መጠን የወዝ አደሩንና የሰፊውን ሕዝብ አብዮታዊ ትግል ሊመራ አይችልም ። ይህ ገና በመራራ ትግል የምንመሠርተው የወዝ አደሩ ፓርቲ ተግባር ነው ።

ያለወዝ አደሩ ፓርቲ አብዮት ግቡን አይመታም የሚለው መፈክር ሳይንሳዊ የሆነ መፈክር ነው ። ይህም ማለት የወዝ አደር ፓርቲ መኖር የአብዮትን ግብ መምታት ፤ የወዝአደር ፓርቲ አለመኖር ደግሞ የአብዮቱ ዞሮ ዞሮ ለጠላት ተጋልጦ መጠቃትንና መቀልበስን ያመለክታል ማለት ነው ። የኢትዮጵያ አብዮታውያን የዚህን ጉዳይ አሳሳቢነት ከተገነዘቡ ቆይተዋል ። ይህንንም በመገንዘብ ለዚህ ለአብዮታችን የሕይወት እስትንፋስ ለሆነው የወዝ አደር ፓርቲ መገንባት አስፈላጊ የሆኑትን ጡቦች በየፊናቸው ሲጥሉ ቆይተዋል ። ከየካቲትም በፊትም ሆነ ከየካቲት በኋላ ልዩ ልዩ ማርክሲስት ሌኒንስት ቡድኖች ተፈጥረው በግንባር ቀደምነት ቢታገሉም እነዚህ ቡተናጥል የሚያደርጉት ትግል እስካልተባበረና እስካልተዋሃደ ድረስ አብዮታችን በምንም ዓይነት ግቡን መምታት እንደማይችል ሁሉም በመደጋገም አስታውቀዋል ። እነዚህ ቡድኖችም ብቻ ሳይሆኑ ወዝ አደሩና በጠቅላላው ሰፊው ሕዝብ የተራማጅ ኃይሎችን አንድነት ለአብዮቱ ዋስትና መሆኑን በመረዳት «የተራማጆች ኅብረት ይጠንክር» እያለ ሲያስተጋባ ቆይቷል ።

በዚህ አቅጣጫ በዚህ በያዝነው የትግል ዓመት የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒንስት ቡድኖች ማለትም መኢሶን ፤ ኢጭአት ፤ የወዝ አደር ሊግ ፤ አብዮታዊ ሰደድና ማሌሪድ የተባሉት ድርጅቶች የትግል ኅብረት ፈጥረው መታገል መጀመራቸው እንደአንድ ታሪካዊ የድል ምዕራፍ የሚቆጠር ሆኖ እናገኘዋለን ። ከዚህም አልፎ በሜይ ዴይ ሠልፍ ወዝ አደሩ የነዚህን ቡድኖች አርማ ይዞ በመውጣት ለፈጠሩት ኅብረት ያለውን ጽኑ ድጋፍ መግለጹ ፤ ኅብረታቸውን አጠንክረው ወደ ውህደት እንዲሸጋገሩ መጠየቁ ይህ በድርጅቶቹ የተወሰደው ርምጃ ትክክለኛና ሰፊው ሕዝብ ያቀፈው የደገፈው መሆኑን ያሳየናል ።

ባለፈው ሜይ ዴይ አከባበር ይህ ለተራማጆች ኅብረት የቆመ ወዝ አደር ሙሉ በሙሉ ከአናርኪስቶችና ከሰርጎ ገቦች የጸዳ መሆኑን አሳይቷል ። ግን ደግሞ ይህ ኃይል ገና በሚገባ ያልተሰበሰበና በይበልጥም መደራጀት ያለበት ኃይል መሆኑንም አሳይቷል ። ወዝ አደሩ ከአምናው ይልቅ ዘንድሮ በይበልጥ የተደራጀ መሆኑን ቢያሳይም የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒንስቶች ገና ብዙ የማንቃትና የማደራጀት ትግል እንደሚጠብቃቸውም በግልጽ የታየ ሐቅ ነው።በመሆኑም ተራማጆች የራሳቸውን ኅብረት በሚገባ አጠንክረው ወደ ወዝ አደሩ በይበልጥ መግባት ይኖርባቸዋል ።

ይህ የተራማጆች ኅብረት እንዲጠነክር የቡድን ስሜት ጨርሶ መወገድ አለበት ። ማርክሲስት ሌኒንስት ድርጅቶች ወደ ወዝ አደሩ ለመግባት በሚያደርጉት ትግል መሻኮት ሳይሆን መተባበር አለባቸው ። በመካከላቸው ያሉትን በሁለተኛ ደረጃ የሚገኙ ቅራኔዎች በሐቀኛ የርእዮተ ዓለም ትግልና በሂስና ግለሂስ መፍታት መቻል አለባቸው ። ምንጊዜም ቢሆን ቡድንን ሳይሆን አብዮቱን ለማስቀደም መጣር አለባቸው ። እነዚህን ሁሉ ለማሟላት እርግጥ ቀላል ነገርና በአንድ አፍታ የሚሆን ነገር አይደለም ። የተራማጆችን ኅብረት ማጠንከር ከአብዮቱ ትግል በምንም ዓይነት የማይነጠል አካል እንደመሆኑ ሁሉ የዚያኑ ያህል መራራና አስቸጋሪ የሆነ ትግል ማካሔድን ይጠይቃል ። ስለዚህም የተራማጆች ኅብረት ይጠንክር የሚሉ ሁሉ ኅብረቱን ለማጠንከር የሚደረገው ትግል እጅግ የተወሳሰበ እንደሆነ መገንዘብና ለዚህ ትግልም መዘጋጀት አለባቸው ።

መሠረታዊው ሐቅ መሳት የለበትም ። በጠቅላላው ፀረ አብዮት ኃይሎች የተራማጆች ኅብረት ለነሱ መቅሰፍት እንደሆነ ያውቃሉ ። ስለሆነም አብዮታውያን የቡድን ስሜት ይጥፉ ሲሉ እነሱ ሰርገው ገብተው የጠባብ ቡድን ስሜትን ያስፋፋሉ ። አብዮታውያን መተማመንን ሲሹ አድኃሪዎች ጥርጣሬን ይነዛሉ ። አብዮታውያን ልዩነቶቻችን ጥቃቅን ናቸው እናቻችላቸው ሲሉ አድኃሪዎችና ሰርጎ ገቦች ልዩነቶችን ለማባባስ ያሴራሉ ። አብዮታውያን ሐቀኛ የርእዮተ ዓለም ትግልን ሲሹ አድኃሪዎች የተራማጆችን ሠፈር በፊውዳል አሉባልታ ለመፍታት ከሰፊው ሕዝብ ሠፈር ሰርገው ገብተው ይፈተፍታሉ ። ባጭሩ አብዮታውያን ኅብረታቸውን ለመገንባት ሲተናነቁ አድኃሪዎች ከሥር ከሥር ሊንዱ ይፍጨረጨራሉ ።

የተራማጆችን ኅብረት ለማጠንከር ፤ ወደ ውህደትም ተሸጋግሮ የወዝ አደሩን ፓርቲ ለመፍጠር «የተራማጆች ኅብረት ይጠንክር» ማለቱ ብቻ አይበቃም ። የዚህ የአብዮታውያን አንድነት ጠር የሆኑትን ኃይሎችም ለመቋቋም ብቁና ዝግጁ መሆን ያስፈልጋል ።

ሰርጎ ገቦችና ከፋፋዮች ይወድማሉ ፤
የተራማጆች ኅብረት ይጠነክራል ፤
የወዝ አደሩ ፓርቲ በትግል ይመሠረታል ፤
ድል የሰፊው ሕዝብ ነው ።